የሰ.መ.ቁ 197432
ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ

ተጠሪ፡- መልካሙ ዳታ ደሴ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 192545 ሐምሌ 27 በቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 670 ድናጋጌን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሡ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በቀን 08/03/2012 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 11፡00 ሠዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ክልል ልዩ ቦታው ሽገር ሕንጻ አካባቢ በሚገኘው የግል ተበዳይ አቶ ብሌን ኀይትኦም ብርክሰትን ክለብ ውስጥ አበባየሁ ከተባለው ካልተያዘ ግብረ አበሩ ጋር በመሆን የበሩን ቁልፍ ፈልቅቀው በመግባት ክለብ ውስጥ የነበረውን 2ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ቃለአብ ቱፋን በተኛበት መጥተው ተጠሪ ቢላዋ በመያዝ ከተንቀሳቀስክ እወጋሃለሁ በማለት ካስፈራራው በኂላ አፉን በፎጣ ሲያፍነው ያልተያዘው ግብረአበሩ ደግሞ በሲባጎ ገመድ አንገቱን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አንቆ ከአልጋው ብረት ጋር በማሰር ራሱን እንዲስት ካደረጉ በኋላ አጠቃላይ ግምቱ ብር 202,000.00 / ሁለት መቶ ሁለት ሺሕ / የሆነ የሙዚቃ ማጫወቻ ሚክሰር፤ የሙዚቃ ማጫወቻ፤ ላፕሮፕ እና ሞባይል በመውሰድ ከተሰወሩ በኋላ በክትትል ተይዞ በምሪት የተገለጹት ንብረቶች ተመላሽ በማድረግ በፈጸመው የውንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ክሱን ሳይቃወም የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅ ዕቃዎቹን የወሰድኩት ድርጅቱ የሠራሁበትን የአምስት ወር ደመወዝ እና የሁለት ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ስለከለከለኝ ነው በማለት መብቱን ጠብቆ ቃሉን መስጠቱ ፍርድ ቤቱ በክሕደት መዝግቦ የዓቃቤ ሕግን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙ የተመሰከረበት በመሆኑ ክሱን እንዲከላከል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም መከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በመግለጹ ፍርድ ቤቱ ተጠሪን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 መሠረት ጥፋተኛ ብሎ በአራት ዓመት ከአምስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በዓቃቤሕግ ምስክሮች በኩል ሳይቀር የተነገረው ተጠሪ በግል ተበዳይ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ እንደነበር እና በወቅቱም ከስራ ተሰናብቶ ባለበት ወቅት ያልተከፈለው ደመወዝ ክፍያ የነበረው መሆኑን ነው፤ ተጠሪ ወሰደ የተባለውን ንብረት ሙሉ ለሙሉ ለግል ተበዳይ የመለሰ ስለመሆኑም አልተካደም፤ ይህም የሚያሳየው የግል ተበዳይን ንብረት ሕገወጥ በሆነ መንገድ የወሰደው ውንብድና ለመፈጸም ሳይሆን ያልተከፈለውን ክፍያ ለማስፈጸም ስለመሆኑ ግልጽ በመሆኑ ተጠሪ የነበረው የወንጀል ሐሳብ ውንብድና ሳይሆን መብቱን በሕገወጥ መንገድ ማስከበር ወንጀል ነው በማለት ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ አንቀጽ ቀይሮ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 431/ለ / ይህ አንቀጽ በስሕተት የተጠቀሰ እና አንቀጽ 436/ለ ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶበታል / መሠረት ጥፋተኛ ብሎ በስድስት ወር ቀላል እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ተጠሪ ከስራ ተሰናብቶ እንደነበር እና ያልተከፈለው ደመወዝ እንደነበረው የተሰጠ የምስክርነት ቃል የለም፤ ተጠሪ ንብረቱን ለግል ተበዳይ መመለሱ የውንብድና ወንጀል ለመፈጸም ሀሳብ እንደሌለው ያሳያል መባሉም ተገቢ አይደለም፤ የተወሰደውን ሐብት የመመለስ ጉዳይ በአድራጊው ፈቃደኝነት የተፈጸመ ቢሆንም የተፈጸመውን ወንጀል አያስቀረውም፤ ተጠሪ ንብረቱን የመለሰው በራሱ ፈቃደኝነት ሳይሆን በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ ነው፤ ስለሆነም እነኚህ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሳይገቡ በስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 ሥር የተመለከተውን ወንጀል በመተላለፍ የውንብድና ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ በሕገ ወጥ መንገድ መብቱን ለማስከበር የተደረገ ድርጊት ነው በሚል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት

ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይሕ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድን ሰዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 የተመለከተዉን የዉንብድና ተግባር ፈጽሟል ብሎ ጥፋተኛ ለማድረግ ድርጊቱ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስቦ፤ የሌላ ሰዉ ንብረት የሆነዉን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ለመዉሰድ እንዲያመቸዉ ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኃላ የገጠመዉን ተቃዉሞ ዉጤታማነት ለማስቀረት ሲል በሌላ ሰዉ ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ዛቻ የፈጸመ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ ይህንን ሰዉ ለመከላከል እንዳይችል ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የተሰሙትን የዓቃቤሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መርምሮ እና መዝኖ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመው በተከሰሰበት ድንጋጌ ላይ የተገለጹትን የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች መሠረት ሳይሆን ያልተከፈለውን ደመወዝ ለማስከፈል ስለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አድራጎት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 ድንጋጌን የሚያቋቁም አይሆንም፡፡
በሌላ በኩል ተጠሪ የሀይል ተግባር በመጠቀም የራሱ ያልሆነውን ንብረት የወሰደ ስለመሆኑ የተረጋጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው አድራጎቱ ሊሸፍነው በሚገባው የሕግ አንቀጽ ሥር ነዉ፡፡ የተጠሪን አድራጎት የሚሸፍነዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ሊከፈለው የሚገባውን ክፍያ ለማግኘት ሲል የባለዕዳው ንብረት የሆነውን ማናቸውንም ተንቀሳቃሽ ዕቃ የወሰደበት እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አልተከፈለኝም የሚለውን ክፍያ እንዲከፈለው ለማድረግ ሲል ድርጊቱን የፈጸመ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው አድራጎቱ በሚሸፍነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ ተጠሪን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ መሠረት ጥፋተኛ በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አልተፈጸመበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 192545 ሐምሌ 27 በቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሰ/ጎ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም